# 427

የዩጎስላቪያ ፡ ሬፑቭሊክ ፡ መንግሥት ፡ ልዩ ፡ መልክተኛና ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሚኒስትር ፡ ክቡር ፡ ሚስተር ፡ ዚዳንኮ ፡ እስታምቡክ ፡ መስከረም ፡ ፳፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከእኩለ ፡ ቀን ፡ በፊት ፡ በገነተ ፡ ልዑል ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ የሹመት ፡ ደብዳቤያቸውን ፡ ሲያቀርቡ ፡ በግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፊት ፡ ቁመው ፡ የተናገሩት ፡ ቃልና ፡ ከግርማዊነ ቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ።

ሀ) የክቡር ፡ ሚኒስትሩ ፡ ንግግር ።

ግርማዊ፡ ሆይ ።

ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትነትዎ ፡ ዘንድ ፡ የዩጎስላቭ ፡ ልዩ ፡ መልክ ተኛ ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሚኒስትር ፡ እንድሆን ፡ በዩጎስላቭ ፡ ፌዴሬ ቲቭ ፡ ፓፑሌር ፡ ሬፑብሊክ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ የተሾሙኩበትን ፡ ደብዳ ቤና ፡ እንዲሁም ፡ ከእኔ ፡ በፊት ፡ የነበሩት ፡ የተጠሩበትን ፡ ደብዳቤ ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ሳቀርብ ፡ ክብር ፡ ይሰማኛል ። *

ዕድለኛ ፡ በሆነው ፡ በዚህ ፡ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ በታላቋና ፡ በጀግናዋ ፡ አገ ርዎ ፡ ውስጥ ፡ ለሚሠራው፡ልማትና ፡ እንዲሁም ፡ ተባብረን ፡ በየጊዜው ፡ የምንሠራው ፡ ሰፊ ፡ ሥራ ፡ ፍሬማ ፡ እንዲሆን ፡ በስተ ፡ ኋላ ፡ በጥብቅ ፡ ለተመሠረተው ፡ ታሪካዊ ፡ ለሆነው ፡ ወዳጅነታችን ፡ በተለይ ፡ ይህን ፡ ክብር ፡ ያለውን ፡ መልክት ፡ ለማከናወን ፡ ስቀበል ፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡ ደስታ ፡ እየተሰማኝ ፡ ነው ።

በሁለታችን ፡ አገሮች ፡ መካከል ፡ ላለው ፡ የጋራ ፡ መግባባትና ፡ ጠንካራ ፡ መሠረት ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ አገልጋዮች ፡ የሚሆኑት ፡ ተመሳሳይ፡ የሆኑ ፡ ጥልቃዊ ፡ ፍቅሮችና ፡ የልብ ፡ ፍጹምነቶች ፡ ናቸው ። እንደዚ ሁም ፡ በመሰለው ፡ የጋራ ፡ መግባባትና ፡ ልባዊ ፡ ፍቅር ፡ ከባድ ፡ ለሆኑት፡ ተግባሮቻችንና ፡ ለወደፊቱ ፡ ወደ ፡ ፍጻሜ ፡ መንገድ ፡ ለምናደርሳቸው ፡ ሁሉ ፡ ሁለቱ ፡ የወዳጅ ፡ ሕዝቦች ፡ ሊያሸንፉት ፡ ይችላሉ ። ይህም ፡ የሚ ሆንበት ፡ ለሰላም ፡ እንደሚከላከሉት ፡ ሁሉ ፡ ለነፃነታቸው ፡ እስከ ፡ መጨ ረሻው ፡ በመታገላቸው ፡ በመንግሥታት ፡ በሕዝቦች ፡ መካከል ፡ ሁሉ ፡ ትክክለኛ ፡ በሆነ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ ስምምነት ፡ እንዲመሠረትና ፡ እንዲሁም ፡ እውነተኛ ፡ የሆነ ፡ ምክንያት ፡ እንዲያሸንፍ ፡ ለመርዳት ፡ ኀይሎቻቸ

* ገጽ ፱፻፴፪ ።



ውንና ፡ ድካሞቻቸውን ፡ ሁሉ ፡ ፍሬ ፡ ባለው ፡ መንገድ ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ለመሰብሰብ ፡ በመቻላቸው ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ በሁለታችን ፡ አገ ሮች ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ወዳጅነትና ፡ የመልካም፡ ግንኙነት ፡ መስፋፋት ፡ ለሁለት ፡ የወዳጅ ፡ መንግሥታት ፡ ከፍ ፡ መባያ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ እንዲ ሁም ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ እርምጃና ፡ ለዓለም ፡ ትግል ፡ ሲባል ፡ በዓለም ፡ ውስጥ ፡ ለሚገኘው ፡ የጦር ፡ ኀይል ፡ ሁሉ ፡ ተጨማሪ ፡ ምስክርም ፡ ነው ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

ግርማዊነትዎ ፡ ከንጉሣዊ ፡ ቤተ ፡ ሰቦችዎና ፡ ከሚኒስትሮችዎ ፡ ጋራ ፡ ዩጐስላቭ ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡ ፡ አድናቆቱንና፡ ከፍ ፡ ያለውን ፡ ፍቅር ፡ ለመግለጽ ፡ በመቻሉና ፡ እንዲሁም፡ወደ ፡ ጀግናው ፡ ሕዝብዎም ፡ ያለውን፡የልብ፡ወዳጅነት፡በማስረዳቱ፡ሕዝቤና ፡ መንግሥቴ ፤ እንዲሁም ፡ ከፕሬዚዳኑ ፡ ጋራ ፡ መላው ፡ አገሬ ፡ ሰላምታ ፡ ለማቅረብ ፡ ምክንያት ፡ በማግኘቱ ፡ ልቤ ፡ በደስታ ፡ ተነክቷል። ወራሪን፡ለመቃወም ፡ ሴኩሪቲ ፡ ኮሌክቲብ ፡ ባልነበረበት ፡ ጊዜ ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ በጣም ፡ የተሠቃ ዩት ፡ ሁለቱ፡መንግሥታቶች፡እንዲጠነክሩ ፡ ዐይነተኛ ፡ ምክንያት ፡ ነው።

ኀይለኛና ፡ እውነተኛ ፡ በሆነ ፡ በጋራ ፡ መረዳዳትና ፡ በተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ደንቦች ፡ መሠረት ፡ በሚከናወኑት ፡ ተግባሮች ፡ በተባብ ሮና ፡ በቍርጣዊ ፡ መደጋገፍ ፡ እውነተኛውንና፡የሚሻለውን ፡ የወደፊት ፡ ዕድል ፡ ለሕዝቦቻችን ፡ ማረጋገጥ ፡ የማይነቃነቅ ፡ ፈቃዳችን ፡ መሆኑን ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ መግለጽ ፡ አለብን ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

ግርማዊነትዎ ፡ አገሬን ፡ በጐበኙበት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ለወደፊት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ መልካም ፡ ዕድል ፡ ከፍ ፡ ያሉ ፡ አክናዋኝና ፡ ታላቅ ፡ መሪ ፡ መሆንዎን ፡ የዩጎስላቪያ ፡ ያገሬ ፡ ሕዝብ ፡ በያለበት ፡ ጥልቅ ፡ በሆነ፡መንፈስ ፡ አድናቆቱን ፡ በተወዳጅ ፡ ግርማዊነትዎ፡ላይ ፡ ስሜቱን ፡ ከልብ ፡ ገልጿል።ለአገርዎ ፡ ነፃነት፡ በታላቅ ፡ ጀግንነት ፡ በተዋጉ ፡ ጊዜ ፡ ሕዝብዎና ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ያደረገው ፡ ተጋድሎ ፡ ከልብ ፡ የማይረሳ ፡ ሆኖ ፡ እንደ፡ተቀረጸው ፡ ሁሉ ፡ እንዲሁም ፡ ግርማዊነትዎ ፡ በዩጎስላቪያ ፡

ውስጥ ፡ በሰነበቱበት ፡ ጊዜ ፡ የተደረጉ ፡ ልዩ ፡ በዓላቶች ፡ በዩጎስላቪያ ፡ ሕዝብ ፡ ልብ ፡ ውስጥ ፡ የማይረሳ ፡ ሆነው ፡ ተቀርጸዋል ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

በሙሉ ፡ ለተከናወኑት፡ መግባባቶችና፡ለተደረጉልኝ ፡ እርዳታዎች ፡ ለግርማዊነትዎ፡ምስጋናዬን፡ ሳቀርብ ፡ እንዲሁም፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ጥልቃዊ ፡ ፍቅርና ፡ ባለፈው ፡ ጊዜ ፡ ለተደረገው ፡ ተጋድሎ ፡ ከልብ ፡ የመነጨ ፡ አድናቆቴን ፡ ስገልጽ ፡ እንዲሁም ፡ ለወደፊቱ ፡ ለሚያንጸባርቀው ፡ ድል ፡ በሁለታችን ፡ ሕዝቦች ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ወዳጅነት ፡ ምክንያት ፡ በሙሉ ፡ ታማኝ ፡ መሆኔን ፡ ለማስረዳት ፡ ያለኝን ፡ መልካም ፡ ፈቃድ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ እንዲቀበሉኝ ፡ በማክበር ፡ እየለመንኩ ፡ ነው ።

ድካሜን ፡ ለሥራ ፡ ለማዋል ፡ በተዘጋጀሁበት ፡ በዚህ ፡ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ የተደረገው ፡ የግርማዊነትዎ ፡ እርዳታና ፡ እምነት ፡ እንዳይለየኝ ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለሁ ።

የዩጎስላቪያ ፡ ሕዝብና ፡ የሬፑብሊኩ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ የተስማሙበትን ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ለንጉሣዊ ፡ ቤተ ፡ ሰብና ፡ ለጀግናው ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ፡ የወዳጅነትና ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ግምት፡ ያለበትን፡ይህን ፡ አዲስ ፡ ምስክር ፡ የሆነውን ፡ ደብዳቤ ፡ መልካም ፡ ፈቃድዎ ፡ ሆኖ ፡ እንዲቀበሉኝ ፡ ግርማዊነትዎን ፡ ስለምን ፡ እንዲሁም ፡ ልዩ ፡ የሆነ ፡ የክብር ፡ ምስጋናዬን ፡ በማቅረብ ፡ ነው ።

* * *

ለ) የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ንግግር ።

ክቡር ፡ ሚኒስትር ።

በንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቤተ ፡ መንግሥታችን ፡ ዘንድ ፡ የወዳጃችን ፡ የዩጎስላቪያ ፡ መንግሥት ፡ ልዩ ፡ መልክተኛና ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሚኒስትር ፡ ሆነው ፡ በመሾምዎ ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ ይለናል ።

በሁለቱ ፡ ሕዝቦች ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ጽኑ ፡ የማይለወጥ ፡ ወዳጅነት ፡ ለጋራ ፡ አሳቦቻችንና ፡ ጥቅሞቻችን ፡ መሠረት ፡ ከመሆኑ ፡ ይልቅ ፡



የሁለቱን ፡ አገሮች ፡ ወዳጅነትና፡ግንኙነት፡ከፍ፡አድርጎ፡የሚያሳይ ፡ ነው ።

በተለይም ፡ አሁን ፡ በቅርቡ ፡ ጊዜ ፡ ለታላቁ ፡ ለዩጎስላቪያ ፡ ሕዝብና ፡ ለከፍተኛው ፡ መሪ ፡ ያደረግነው፡ መጐብኘት ፡ በሁለቱ ፡ አገሮች ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ወዳጅነትና ፡ መተሳሰር ፡ ግልጥና ፡ የጠነከረ ፡ መሆኑን ፡ የሚመሰክር ፡ ነው ። በዩጎስላቪያ ፡ በነበርንበት ፡ ጊዜያት ፡ ስመ ፡ ጥሩውን ፡ የዩጎስላቪያ ፡ ሕዝብና ፡ ታላቁ ፡ መሪው ፡ በየቀኑ ፡ ያደረጉልንን ፡ መልካም ፡ አቀባበል ፡ ለሕዝቡና፡ ለተከበሩት፡ መሪው ፡ የነበረንን ፡ አድናቆት ፡ ያረጋገጠ ፡ ሆኗል ። በዩጎስላቪያ ፡ ውስጥ ፡ እየተዘዋወርን ፡ ባደረግነው ፡ መጐብኘት ፡ ጊዜያት ፡ በገለጠልን ፡ የደስታ ፡ ስሜትና ፡ ባደረገልን ፡ መልካም ፡ አቀባበል ፡ ልባችን ፡ በጥልቅ ፡ ተነክቷል ።

በሁለቱ ፡ አገሮች ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ወዳጅነት ፡ የበለጠ ፡ ለማስፋፋትና ፡ ለማደርጀት ፡ በሚያደርጉት ፡ ጥረትና ፡ የሥራ ፡ መግባባት ፡ እርዳታችን ፡ የማይጓደልብዎ ፡ መሆኑን ፡ ሊተማመኑ ፡ ይችላሉ ።

ይህን ፡ አጋጣሚ ፡ ጊዜ ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ ለታላቁ ፡ ክብር ፡ የዩጎስላቪያ ፡ መሪ ፡ ለማርሻል ፡ ቲቶ ፡ የወዳጅነት ፡ ሰላምታችንን ፡ እንዲያደርሱልንና ፡ ለዩጎስላቪያ ፡ ሕዝብ ፡ ብልጽግና ፡ ደኅንነት ፡ ያለንን ፡ መልካም ፡ ምኞት ፡ እንዲገልጹልን ፡ እንጠይቅዎታለን ።

---

# 428

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የእንግሊዝን ፡ አገር ፡ እንዲጐበኙ ፡ ከግርማዊት ፡ ንግሥት ፡ ኤልሳቤጥ ፡ የተላከላቸውን ፡ ጥሪ ፡ መሠረት፡ በማድረግ ፡ ወደዚሉንዶን ፡ ለመሄድ ፡ የክብር ፡ ተከታዮቻቸውን፡ አስከትለው ፡ መስከረም፡ ፳፰ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፯፡ ዓ ፡ ም ፡ ማክሰኞ ፡ በ፰ ፡ ሰዓት ፡ ተሩብ ፡ ከአዲስ ፡ አበባ ፡ በንሥረ ፡ ኢትዮጵያ ፡ አውሮፕላን ፡ ተነሡ ። ከእኩለ ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ በ፲፩ ፡ ሰዓት ፡ በሱዳን ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ ከምትገኘው ፡ ዋዲሐልፋ ፡ ከምትባለው ፡ ከተማ ፡ ደረሱ ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ የሱዳን ፡ መንግሥት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ የክብር ፡ አቀባበል ፡ አድርገውላቸው ፡ በዚሁ ፡ ከተማ ፡ በተለይ ፡ በተዘጋጀው ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ አደሩ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የሱዳን ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትር ፡ ክቡር ፡ አልሳይድ ፡ እስማኤል ፡ አልአዝሃሪ ፡ የተናገሩት ፡ የመልካም ፡ ምኞት ፡ መግለጫ ፡ ቃልና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠው ፡ መልስ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ነው ።

ሀ) የክቡር ፡ አልሰይድ ፡ እስማኤል ፡ አልአዝሃሪ ፡ ንግግር ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

በሱዳን ፡ መንግሥትና ፡ በወንድሞቼ፡ በሱዳን ፡ ተወላጆች ፡ ስም

ሆኜ ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ እንኳን ፡ ደኅና ፡ መጡ ፡ በማለት ፡ ይህችን ፡ የደስታ ፡ ቃሌን ፡ ሳቀርብልዎ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ሊሄዱ ፡ ለተዘጋጀው ፡ መንገድ ፡ አምላክ ፡ በሰላም ፡ ጠብቆ ፡ ወደ ፡ ውዲቱ ፡ ኢትዮጵያ ፡ አገርዎ ፡ እንዲመልስዎ ፡ ልባዊ ፡ ጸሎቴ ፡ ነው ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

ከፍ ፡ ብዬ ፡ በጠቀስኩት ፡ ቃል ፡ መሠረት ፡ በራሴና ፡ በሱዳን ፡ ወንድሞቼ ፡ ስም ፡ ሆኜ ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ሳቀርብ ፡ ዕድሌ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ መሆኑን ፡ ስገምተው ፡ ለወደፊቱም ፡ ለኢትዮጵያ ፡ አገርዎ ፡ መልካም ፡ ምኞቴን ፡ አልነሳም ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

አዲስ ፡ በተሰጠው ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ሱዳን ፡ ከተወላጆቹና ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ጎረቤት ፡ አገሩ ፡ ጋራ ፡ ለወደፊቱ ፡ የፍቅር ፡ መተሳሰር ፡ ለሁለት ፡ አገሮቻችን ፡ ጠቃሚ ፡ የሆነ ፡ ደኅና ፡ ሐሳብ፡ በመሆኑ ፡ ሕዝቡም ፡ በፍቅርና ፡ በደኅና ፡ ስምምነት ፡ እንዲኖር ፡ በተስፋ ፡ የምንጠባበቅ ፡ ነን ፡ ብዬ ፡ በማመን ፡ ወደረኛ ፡ ለሌለው ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ሥልጣን ፡ በታላቅ ፡ ትሕትና ፡ እገልጻለሁ ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

የሱዳንና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ወዳጅነት ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ የተሳሰረ ፡ ነው ። ምክንያቱም ፡ ከአንድ ፡ ዐባይ ፡ ውሃ ፡ ስለሚጠጡና ፡ ያባይንም ፡ ውሃ ፡ ሲመለከቱት፡ የሁለት ፡ አገሮች፡ ፍቅር ፡ የማይዘነጋ ፡ የማይረሳ ፡ መሆኑን ፡ አጥብቀው ፡ የሚገነዘቡት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፤ በራሴና ፡ በሱዳን ፡ ስም ፡ ሆኜ ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ ረጅም ፡ ዕድሜ ፡ ለጎረቤታችን ፡ ለኢትዮጵያ ፡ አገርዎ ፡ ሙሉ ፡ ሰላምና ፡ መልካም ፡ ዕድል ፡ ከዘመኑ ፡ ሥልጣኔ ፡ እርምጃ ፡ ጋራ ፡ እንድትራመድ ፡ እመኛለሁ ።

* * *

ለ) ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ።

ለክቡር ፡ አልሰይድ ፡ እስማኤል ፡ አልአዝሃሪ ፡ የሱዳን ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትር ፤



ወደ ፡ ኤውሮፓ ፡ ጕዟችንን ፡ ስንጀምር ፡ በዚች ፡ ለኛ ፡ ታሪካዊ ፡ የሆነች ፡ ቦታ ፡ በዋዲ ፡ ሐልፋ ፡ ስናልፍ ፡ ክቡርነትዎ ፡ ስለኛና ፡ ስለ ፡ አገራችን ፡ ለገለጧቸው ፡ መልካም ፡ የወዳጅነት ፡ ቃሎች ፡ ከልብ ፡ እናመሰግንዎታለን ።

እኛን ፡ ለመቀበል ፡ የላኩዋቸው፡ ክቡራን፡ ሚኒስትሮችዎና፡ የዋዲ ፡ ሐልፋ፡ ሕዝብ ፡ ስላደረጉልን ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ አቀባበል ፡ ደስታችንን ፡ ልንገልጥልዎ ፡ እንወዳለን ። በሁለቱ ፡ አገሮቻችን ፤ መካከል ፡ የቈየው ፡ ወዳጅነት ፡ እየለማና ፡ እየደረጀ ፡ እንዲሄድ ፡ በገለጹት ፡ ምኞት ፡ ተካፋይ ፡ መሆናችንን ፡ እንገልጽልዎታለን ።

የዛሬ ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ያገራችንን ፡ ነፃነት ፡ ለማስመለስ፡ በስደት ፡ ከኖርንበት ፡ ከእንግሊዝ ፡ አገር ፡ ስንመለስ ፡ መጀመሪያ ፡ ያረፍንበት ፡ የጦር ፡ ዐቅዶችንና ፡ ድርጅቶቻችንን ፡ የወሰንበት ፡ ዋዲ ፡ ሐልፋ ፡ ስለ ፡ ሆነች ፡ ለኛ ፡ ታላቅ፡ መታሰቢያ፡ ያላት ፡ ከተማ ፡ ነች ።

# 429

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፤ መስከረም ፡ ፳፮ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ በተላከላቸው ፡ አትላንታ ፡ በተባለ ፡ ልዩ ፡ የክብር ፡ አውሮፕላን ፡ ከጧቱ ፡ ባ፩ ፡ ሰዓት ፡ ከዋዲ ፡ ሐልፋ ፡ ተነሥተው ፡ ማታ ፡ ባ፲ ፡ ሰዓት ፡ ማልታ ፡ ደሴት ፡ ደረሱ ። በዚያም ፡ አገረ ፡ ገዢው ፡ ሰር ፡ ሮበር ፡ ሌይ ፡ ኮክና ፡ የማልታ ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትር ፡ በክብር ፡ ተቀብለዋቸው ሳንት ፡ አንቶኒና ፡ በተባለው ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ አደሩ ።

መስከረም ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የማልታን ፡ ደሴት ፡ አካባቢዎችና ፡ የሥራ ፡ ክፍሎችን ፡ ሲጐበኙ ፡ ከዋሉ ፡ በኋላ ፤ አገረ ፡ ገዢው ፡ በባሊታ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ታላቅ ፡ የምሳ ፡ ግብዣ ፡ አደረጉላቸው ። እንዲሁም ፡ በዚሁ ፡ ቀን ፡ ማታ ፡ የእንግሊዝ ፡ የሜዲቴራኒያን ፡ የጦር ፡ መርከቦች ፡ ጠቅላይ ፡ አዛዥ ፡ አድሚራል ፡ ሎርድ ፡ ማውንትባትን፡ በመኖሪያ ፡ ቤታቸው ፡ ታላቅ ፡ የራት ፡ ግብዣ ፡ አደረጉላቸው ።

መስከረም ፡ ፳፰ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ጧት ፡ በእንግድነት ፡ ካረፉበት ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ተነሥተው ፡ ከክብር ፡ ተከታዮቻቸው ፡ ጋራ ፡ ጋምቢያ ፡ በተባለ ፡ የእንግሊዝ ፡ የጦር ፡ መርከብ ፡ ተሳፍረው ፡ ወደ ፡ ሎንዶን ፡ ጕዟቸውን ፡ ቀጠሉ ።

ጥቅምት ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ኀሙስ ፡ ከጧቱ ፡ በ፩ ፡ ሰዓት ፡ ተሩብ ፡ ፖርትስመት ፡ ከተባለ ፡ ወደብ ፡ ደርሰው ፡ የእንግሊዝን ፡ መሬት ፡ ሲረግጡ ፡ ልዑል ፡ የግሎስተር ፡ ዱክ ፡ በታላቅ ፡ ክብር ፡ ተቀበሏቸው ። በወደቡ ፡ ላይ ፡ የተደረገው ፡ ያቀባበል ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላም ፡ የፖርትስመትን ፡ ከተማ ፡ ጐብኝተው ፡ በማዘጋጃ ፡ ቤቱ ፡ አዳራሽ ፡ ውስጥ ፡ ሳሉ ፡ የከተማው ፡ ከንቲባ ፡ ስለ ፡ ግርማዊነታቸው ፡ እንግድነት ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ንግግር ፡ አደረጉ ።

ሀ) የፖርት ፡ ስመት ፡ ከንቲባ ፡ ንግግር ።

ግርማዊነትዎ ፡ ለዚህ ፡ ለከተማችን ፡ እንግዳው ፡ አይደሉም ። በጠርነቱ ፡ ጊዜ ፡ ውሀጥ ፡ ከዚህ ፡ ከተማ ፡ ከፖርት ፡ ስመት ፡ ውስጥ ፡ ቈይተው ፡ በእነዚህ ፡ ወራት ፡ የነበሩትን ፡ አደጋዎችና ፡ ፈተናዎች ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ እንደተካፈሉ ፡ እናስታውሳለን ።

---

# 430

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ጥቅምት ፡ ፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በ፫ ፡ ሰዓት ፡ ከክብር ፡ ተከታዮቻቸው ፡ ጋራ ፡ በልዩ ፡ ባቡር ፡ ተሳፍረው ፡ ከፖርት ፡ ስመት ፡ ወደ ፡ ሎንዶን ፡ ተጓዙ ። በ፬ ፡ ሰዓት ፡ ሎንዶን ፡ በቢክቶሪያ ፡ ጣቢያ ፡ ሲደርሱ ፡ ግርማዊት ፡ የእንግሊዝ ፡ ንግሥት ፡ ኤልሳቤጥና ፡ ባለቤታቸው ፡ የኤድንቨራው ፡ መስፍን ፡ ተቀበሏቸው ።

ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ከንግሥቲቱ ፡ ጋራ ፡ በአንድ ፡ የክብር ፡ ሠረገላ ፡ ተቀምጠው ፡ ወደ ፡ በኪንግሃም ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ሄዱ ።

ከእኩለ ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ በ፲፩ ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ በሴንት ፡ ጀምስ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ተገኝተው ፡ ሳሉ ፡ የሎንዶን ፡ ካውንቲ ፡ ካውንስል ፡ ፕሬዚዳንትና ፡ የዌስት ፡ ሚኒስቴር ፡ ሲቲ ፡ ከንቲባ ፡ እንኳን ፡ በደኅና ፡ መጡ ፡ የሚል ፡ ያቀባበል ፡ መግለጫ ፡ ንግግር ፡ ስላደረጉላቸው ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ መልስ ፡ ሰጡ ። ደግሞም ፡ ለዌስት ፡ ሚኒስቴር ፡ አንድ ፡ የደስታ ፡ መግለጫ ፡ ቃል ፡ በጽሑፍ ፡ እንዲሰጥ ፡ ደረጉ ።

ሀ) ለከንቲባው ፡ ንግግር ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ።

የተከበሩ ፡ ፕሬዚዳንት ፤

የተከበሩ ፡ ከንቲባ ፤

ባለውለታችን ፡ የሆነውን ፡ ይህን ፡ አገር ፡ እንደ ፡ ገና ፡ መጥቼ ፡ ለመጐብኘት ፡ በመቻሌ ፡ ታላቅ ፡ ደስታ ፡ ይሰማኛል ። የተዋበችና ፡ ታሪካዊ ፡ አገራችሁን ፡ ስጐበኝ ፡ በውነቱ ፡ ዛሬ ፡ የመጀመሪያ ፡ ጊዜዬ ፡ አይደለም ። የእንግሊዝን ፡ አገር ፡ መጀመሪያ ፡ ከጐበኘሁ ፡ እነሆ ፡ ዛሬ ፡ ሠላሳ ፡ ዓመት ፡ ነው ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የተደረገልኝ ፡ የጋለ ፡ አቀባበል ።



የሰጠኝ ፡ ስሜት ፡ ከዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ በሕዝቤ ፡ ላይ ፡ የደረሰው ፡ ሥቃይ ፡ ልቤን ፡ በኀዘን ፡ ሞልቶት ፡ በትክክለኛ ፡ ፍርድና ፡ ለኮሌክቲብ ፡ ሴክዩሪቲ ፡ ያለ ፡ አንድ ፡ ረዳት ፡ ብቻዬን ፡ የጀመርሁትን ፡ ትግል ፡ ለመቀጠል ፡ ስደትን ፡ መርጬ ፡ ወደዚህ ፡ አገር ፡ ስመጣ ፡ በሎንዶን ፡ ጐዳናዎች ፡ ሳልፍ ፡ የተደረገልኝ ፡ አቀባበል ፡ የሰጠኝ ፡ ስሜት ፡ ከመጀመሪያው ፡ ስሜት ፡ የተቀነሰ ፡ አልነበረም ። ለኔና ፡ ለአገሬ ፡ ብርቱ ፡ የሞራል ፡ ደገፋና ፡ መጽናናት ፡ አስፈላጊያችን ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ ታሪካዊ ፡ በሆኑት ፡ ጐዳናዎቻችሁ ፡ ሳልፍ ፡ የሎንዶን ፡ ሕዝብ ፡ ያደረገልኝ ፡ መልካም ፡ አቀባበል ፡ ለኀዘኔ ፡ ታላቅ ፡ ግምት ፡ ያለው ፡ መጽናኛ ፡ ሆኖኝ ፡ ነበር ። በእንግሊዝ ፡ የታመነ ፡ እርዳታና ፡ መሥዋዕትነት ፡ የተወደደችውን ፡ አገሬን ፡ ነፃ ፡ ለማውጣት ፡ እስከቻልሁበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ በነበረው ፡ የአምስት ፡ ዓመት ፡ ትግል ፡ ያደረጋችሁልኝ ፡ እርዳታ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ተስፋ ፡ ያለው ፡ መስሎ ፡ ያልታየውን ፡ ሁኔታ ፡ በብርታት ፡ ለመከታተል ፡ ለመንፈሴ ፡ ጉልበት ፡ ሆኖኝ ፡ ነበር ።

የዛሬ ፡ ዐሥራ ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡ በነዚያ ፡ በመከራ ፡ ቀኖች ፡ የሎንዶን ፡ ከተማ ፡ ያደረገችልኝ ፡ አቀባበልና ፡ እናንተም ፡ በስደቴ ፡ ዘመን ፡ ያሳያችሁኝ ፡ መልካም ፡ የእንግዳ ፡ ተቀባይነት ፡ መንፈስ ፡ ለናንተና ፡ ለታላቁ ፡ ከተማችሁ ፡ በማይቀዘቅዘው ፡ ፍቅራችን ፡ ውስጥ ፡ ስፍራ ፡ አስገኝቶልታል ። በችግሬ ፡ ጊዜ ፡ ያገኘሁት ፡ መልካም ፡ አቀባበል ፡ አሁንም ፡ እንደ ፡ ገና ፡ በዚህ ፡ ዕድለኛ ፡ በሆነው ፡ አመጣጥ ፡ የበለጠ ፡ አድርጋችሁ ፡ ስለ ፡ አሳያችሁኝ ፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡ ምስጋናዬን ፡ እገልጥላችኋለሁ ።

* * *

ለ) ለዌስት ፡ ሚኒስቴር ፡ ከንቲባ ፡ በጽሑፍ ፡ የተሰጠ ፡ የደስታ ፡ መግለጫ ።

የተከበሩ ፡ ከንቲባ ።

የዚህ ፡ ታላቅ ፡ ከተማ ፡ ነዋሪ ፡ ከሆነው ፡ ሕዝብ ፡ የተደረገልኝ ፡ መልካም ፡ አቀባበል ፡ ልቤን ፡ ነክቶታል ።

የዛሬ ፡ ፲፰ ፡ ዓመት ፡ በደረሰብኝ ፡ ችግር ፡ ጊዜያት ፡ ያደረጋችሁል ኝን ፡ መልካም ፡ የእንግድነት ፡ አቀባበል ፡ ሁል፡ጊዜ ፡ አስታውሳለሁ ። በመካከላችን ፡ ያለው ፡ መግባባትና ፡ በጎ ፡ አስተያየት ፡ ዘላቂ ፡ የሆነ ውን ፡ ወዳጅነታችንን ፡ የተቃረበና ፡ የደረጀ ፡ ለማድረጉ ፡ በንግግርዎ ፡ ከገለጡዋቸው ፡ መልካም ፡ ቃሎች ፡ የተሻለ ፡ ምስክር ፡ አይገኝለትም ።

እነዚህ ፡ ታሪካዊ፡የሆኑ ፡ ሕንፃዎች ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ድምፃቸውን ፡ ለማሰማት ፡ የማይችሉ ፡ ቢሆኑ ፡ ቀድሞ ፡ የነበራችሁንና ፡ ወደ፡ፊትም ፡ የናንተ ፡ የሆነውን ፡ ታላቅ ፡ ክብርና ፡ ታሪክ ፡ የሚያስረዱ ፡ ናቸው ። እኔም ፡ በዛሬ ፡ ቀን ፡ በነዚህ ፡ ሕንፃዎች ፡ ውስጥ ፡ በመገኘቴና ፡ እነዚ ህን ፡ የወዳጅነት ፡ ምልክቶች ፡ ከናንተ ፡ ለማግኘት ፡ በመቻሌ ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ ብሎኛል ።

የኔ ፡ ይህን ፡ የወዳጅ ፡ አገር ፡ መጐብኘት ፡ በመካከላችን ፡ ያለ ውን ፡ መግባባት ፡ የበለጠ ፡ ለማስፋፋትና ፡ ለማደራጀት ፡ እንዲያገለግል፡ ተስፋዬ ፡ ነው ።

---

# 431

ጥቅምት ፡ ፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ኀሙስ ፡ ከማታው ፡ በ፰ ፡ ሰዓት ፡ ስለ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ክብር ፡ በበኪንግሃም ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ በተደረገው ፡ ታላቅ ፡ የእራት ፡ ግብዣ ፡ ላይ ፡ ግርማዊት ፡ የእንግሊዝ ፡ ንግሥት ፡ የተናገሩት ፡ ቃልና ፡ ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ።

ሀ) የግርማዊት ፡ ንግሥት ፡ ኤልሳቤጥ ፡ ንግግር ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

ወደ ፡ መናገሻ ፡ ከተማዬና ፡ አገሬ ፡ እንኳን ፡ በደኅና ፡ ገቡ ። የጥን ታዊት ፡ ክርስቲያን ፡ አገር ፡ንጉሠ፡ነገሥትን ፡ ወሰን ፡ በሌለው ፡ ደስታ ፡ እንቀበላለን ። ጥንታዊት ፡ የክርስቲያን ፡ አገርዎ ፡ ከኛ ፡ ቤተ ፡ ክርስ



ቲያንና ፡ ከሌሎችም ፡ የክርስቲያን ፡ አገሮች ፡ ጋራ ፡ ግንኙነት ፡ አላት ። ነፃ ነትዋን፡በመጀመሪያ ፡ መልሳ ፡ ያገኘችውን ፡ አገር ፡ ንጉሠ፡ ነገሥት ፡ በደ ስታ ፡ እንቀበልዎታለን ። በግርማዊነትዎ ፡ ትጉህ ፡ መሪነት ፡ ከጦርነቱ ፡ ወዲህ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ አስገራሚ ፡ የሥልጣኔ ፡ እርምጃ ፡ አድርጎ ዋል ። የኢትዮጵያን ፡ ነፃነት ፡ ለመመለስ ፡ ከአርበኞችዎ ፡ ጋራ ፡ ሆኖ ፡ የኔ ፡ አገር ፡ በሠራው ፡ ሥራ ፡ በጣም ፡ እደሰትበታለሁ ። በጦርነቱም ፡ ጊዜ ፡ በሁለቱ ፡ አገሮችና ፡ በወታደሮቻችን ፡ መሐል ፡ ጥልቅ ፡ ወዳጅ ነት ፡ ተመሥርቶ ፡ ነበር ።

ይህም ፡ ወዳጅነት ፡ በሰላም ፡ ጊዜ ፡ እየጠነከረና ፡ እየተሳሰረ ፡ እንደ ሚሄድ ፡ የልብ ፡ ምኞቴ፡ ነው ። የግርማዊነትዎም ፡ ምኞት ፡ እንደ፡ሆነ ፡ አምናለሁ ።

ግርማዊነትዎ ፡ በዚህ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ እንግዳ ፡ አይደሉም ። አገ ርዎ ፡ በተወረረች ፡ ጊዜ ፡ መጥተው ፡ ነበር ። እንግሊዝ ፡ አገርም ፡ በሚቀ መጡበት ፡ ቀናት ፡ ልክ ፡ ባገርዎ ፡ እንዳሉ ፡ አድርገው ፡ እንዲያስቡት ፡ እጠይቅዎታለሁ ። ባለቤቴና ፡ እኔ ፩ ግርማዊት ፡ እቴጌን ፡ እዚህ ፡ ለመቀ በል ፡ ባለመቻላችን ፡ ጥልቅ ፡ ኀዘን ፡ ይሰማናል ። ሙሉ ፡ ጤናን ፡ አግኝ ተው ፡ ወደፊቱ ፡ እንደሚጐበኙን ፡ ተስፋ ፡ አለኝ ።

የግርማዊነትዎን ፡ ልጅ ፡ ልዑል ፡ መስፍን ፡ የሐረርን ፡ ዱክ ፡ በደ ስታ ፡ እንቀበላቸዋለን ። ልዑልነታቸው ፡ ይኸንን ፡ አገር ፡ ያውቁታል ። እሳቸውንም ፡ በማየታችን ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ ብሎናል ።

ግርማዊነትዎ ፡ የኦፊሲዬል ፡ ጕብኝትዎን ፡ ከጨረሱ ፡ በኋላ ፡ ለጥ ቂት ፡ ቀን ፡ እዚህ ፡ ስለሚቈዩ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ ይለኛል ። በጥቂቱም ፡ ቀናት ፡ ውስጥ ፡ የእንግሊዞችን ፡ አኗኗርና ፡ አገራችንንም ፡ እየዞሩ ፡ ለማየት ፡ ይችላሉ ። በሄዱበትም ፡ ቦታ ፡ አስደሳች ፡ አቀባበል ፡ እንደሚ ደረግልዎ ፡ እርግጠኛ ፡ ነኝ ። በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ላገራቸው ፡ ነፃነት ፡ ላስገ ኙና ፡ በሰላምም ፡ ጊዜ ፡ ለአገራቸውና ፡ ለሕዝባቸው ፡ ብልጽግና ፡ ሀብ ትና ፡ ብርሃንን ፡ ላስገኙ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ምስጋና ፡ የተሞላበትን ፡ አድ ናቆቱን ፡ ለማቅረብ ፡ ሕዝቤ ፡ ይቸኵላል ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

በምናብብበትና ፡ በምንበለጽግባቸው ፡ የወዳጅነት ፡ መንፈስና ፡ የጋራ ፡ ሐሳቦች ፡ ግብ ፤ ለግርማዊነትዎና ፡ ለግርማዊት ፡ ጤና ፤ ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሀብትና ፡ ደስታ ፡ ጽዋዬን ፡ አነሣለሁ ።

* * *

ለ) የግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንግግር ።

ግርማዊት ፡ ሆይ ።

ግርማዊትነትዎ ፡ በተናገሩዋቸው ፡ መልካም ፡ የእንግድነት ፡ አቀባበል ፡ በተመላባቸው ፡ ቃሎችና ፡ ስለኔም ፡ ስለራሴ ፡ በገለጹዋቸው ፡ የልግስና ፤ ስሜቶች ፡ ልቤ ፡ በጥልቅ ፡ ተነክቷል ። ምንም ፡ እንኳ ፡ ይህችን ፡ የተዋበች ፡ አገርዎን ፡ የረገጥሁት ፡ ከጥቂት ፡ ሰዓቶች ፡ በፊት ፡ ቢሆን ፡ ግርማዊትነትዎ ፡ የተናገሩዋቸው ፡ ቃሎች ፡ የዛሬ ፡ ፴ ፡ ዓመት ፡ ከዚህ ፡ አገር ፡ ከመሄዴ ፡ በፊት ፡ የተደረገልኝን ፡ አስተያየት ፡ የሚያሳስቡኝ ፡ ሆነዋል ።

ወደ ፡ ግርማዊትነትዎ ፡ አገር ፡ ስመጣ ፡ ዛሬ ፡ መጀመሪያ ፡ ጊዜዬ ፡ አይደለም ። የዛሬ ፡ ሠላሳ ፡ ዓመት ፡ ይህን ፡ አገር ፡ ለመጐብኘት ፡ ስመጣ ፡ ወደዚህ ፡ ታላቅ ፡ ከተማ ፡ እንደ፡ደረስሁ ፡ በኦፊሲዬል ፡ የተቀበሉኝ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የዮርክ ፡ መስፍን ፤ ኋላ ፡ ግን ፡ ጆርጅ ፡ ፮ኛው ፡ የነበሩት ፡ ግርማዊ ፡ አባትዎ ፡ ነበሩ ። የተወደዱት ፡ ንጉሥ ፡ ያደረጉልኝ ፡ የወዳጅነት ፡ አቀባበል ፡ ከንጉሣዊ ፡ ባሕሪያቸው ፡ ጋራ ፡ የተዋሐደ ፡ መሆኑ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ትዝ ፡ ይለኛል ።

ባለፉት ፡ ሠላሳ ፡ ዓመቶች ውስጥ ፡ በአገሬ ፡ ላይ ፡ ደርሶ ፡ የነበረው ፡ መሪር ፡ የሆነ ፡ ረጅም ፡ የመከራ ፡ ጊዜያትና ፤ እኔም ፡ ራሴ ፡ ባሳለፍሁት ፡ የስደት ፡ ዘመን ፡ ሲያጽናናን ፡ የቈየው ፡ የንጉሣዊ ፡ ቤተ ፡ ሰብዎ ፡ መልካም ፡ አስተያየትና ፡ የታላቁ ፡ የእንግሊዝ ፡ ሕዝብ ፡ ወዳጅነትና ፡ እንግዳ፡ ተቀባይነት ፡ ነው ። እኔና ፡ ሕዝቤ ፡ ብቻችንን ፡ ያለ፡ አንድ ፡ ረዳት ፡ ባደረግነው ፡ ተጋድሎ ፡ ደጋፊያችን፡የነበረው ፡ የእንግሊዝ ፡ ንጉሣዊ ፡ ቤተ ፡ ሰብና ፡ የእንግሊዝ ፡ ሕዝብ ፡ ፍቅር ፡ ብቻ ፡ ነበር ። ይህ ፡ ወዳጅነትና ፡ ታማኝነት ፡ የኛን ፡ የማይጠፋ ፡ ውለታና ፡ ወዳጅነት ፡ አትርፎዋል ።



የግርማዊትነትዎ፡ እርዳታና ፡ የልጆቻቸው ፡ ደም ፡ ከልጆቻችን፡ደም ፡ ጋራ ፡ በኢትዮጵያ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ያፈሰሰው ፡ የእንግሊዝ ፡ ሕዝብ ፡ ታማኝነት ፡ በሁለቱ ፡ አገሮቻችን ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ወዳጅነትና ፡ መተሳሰብ ፡ እንደ ፡ ተቀደሰ ፡ አደራ ፡ ተጠብቆ ፡ እንዲኖር ፡ አድርጎታል ።

እነዚሁም ፡ የእንግሊዝ ፡ ጀግኖች ፡ በአገራቸው ፡ መሬትና ፡ ደግሞ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ነፃነት ፡ ለማስመለስ ፡ በአገራችን ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ የፈጸሙዋቸው ፡ ክብር ፡ የመላባቸው ፡ ተጋድሎዎች ፡ ናቸው ።

ምንም ፡ እንኳ ፡ የታሪኩ ፡ ዘመን ፡ ኀዘንና ፡ መሥዋዕትነትን ፡ የሥራ ፡ ፍሬንና ፡ ክብርን ፡ እያፈራረቀ፡ ያስገኘ ፡ ቢሆን ፡ መጨረሻው ፡ ዘመን ፡ ብሩህና ፡ ታላቅ ፡ ተስፋ ፡ ያለው ፡ ለመሆኑ ፡ ጸጋ ፡ የተሰጣቸው ፡ የወጣቷ ፡ ንግሥት ፡ እጅግ ፡ ከፍ ፡ ባለው ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ መቀመጥ፡ የሚበቃ ፡ ምልክት ፡ ነው ።

ግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ በሚያሳዝን ፡ አጋጣሚ ፡ በጤናዋ ፡ ምክንያት ፡ በዚህ ፡ ለመገኘት ፡ ለመምጣት ፡ ባለመቻሏ ፡ እጅግ ፡ ታዝናለች ፤ ይህንም ፡ ኀዘኗን ፡ ለግርማዊት ፡ ንግሥት ፡ እንድገልጽላት ፡ ለምናኛለች ።

በታላቅ ፡ አክብሮትና ፡ አድናቆት ፡ ለምንመለከታቸው ፡ ለግርማዊት ፡ ንግሥት ፡ ጤና ፡ ጽዋችንን ፡ እናነሣለን ።

---

# 432

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ጥቅምት ፡ ፳ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በ፮ ፡ ሰዓት ፡ ከክብር ፡ ተከታዮቻቸው ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ጊልድ ፡ ሆል ፡ ሄዱ ። የሎንዶን ፡ ከንቲባ ፡ በጊልድ ፡ ሆል ፡ አዳራሽ፡ ስለ፡ ግርማዊነታቸው ፡ ክብር ፡ ባደረጉት ፡ ግብዣ ፡ ላይ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የተናገሩት ፡ ቃል ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ነው ።

የተከበሩ ፡ ከንቲባ ።

የእንግሊዝን ፡ አገር ፡ በኦፊሲዬል ፡ ለመጐብኘት ፡ በመጣሁበት ፡ በዚህ ፡ ቀን ፡ ስለ ፡ ተደረገልኝ ፡ መልካም ፡ አቀባበል ፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡ ደስታ ፡ ተሰምቶኛል ። ከአገሬ ፡ በወጣሁበት ፡ ዘመን ፡ በእንግሊዝ፡ ሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ መልካም፡ አቀበባል ፡ አግኝቼ ፡ ከቈየሁባቸው ፡ ከነዚያ ፡